
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ
የዱር እንስሳት ጥናት፣ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም
ስራ ሂደት
የጉና ተራራ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ
ህጋዊ እውቅና ለማስጠት የተዘጋጀ
ደጋፊ ሰነድ
ጥር 2006
ባህርዳር

ማውጫ

1.መግቢያ 1

1.1. አጠቃላይ ሁኔታ 1

2.የደጋፊ ሰነዱ ዓላማዎች 2

2.1. አጠቃላይ ዓላማ 2

2.2.ዝርዝር ዓላማዎች 2

3.የአየር ንብረትና መገኛ 2

3.1.መገኛና ስፋት 2

3.2.አግሮ ኢኮሎጂና የአየር ንብረት፣ 3

4.ብዝሐ ህይወትና ብርቅይነት 3

4.1. አጥቢ እንስሳት 4

4.2. አእዋፋት 4

4.3. የእፅዋት ሽፋንና ዓይነት 5

5. በተፈጥሮ ሃብቱ አካባቢ ያሉ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ኃይማኖታዊ የቱሪዝም ሃብቶች ሁኔታ 5

6. በታሳቢ የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የሚኖሩ ህዝቦች አኗኗርና የሚያደርሱት ተፅዕኖ 7

6.1. የአካባቢው ነዋሪዎች ሁኔታ 7

6.2. በተፈጥሮ አካባቢው ላይ የሚታዩ ጫናዎች/ተጽዕኖዎች 8

7. የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የሚኖረው ጠቀሜታ 9

8. የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የወደፊት የጥበቃ ሁኔታ 11

9. ማጠቃለያ 12

10. ዕዝል 15

10.1 የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ወሰን ዝርዝር መግለጫ 15

10.2. የጉና ተራራ ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ የክለላ ካርታ 23

10.3. የፀደቀ የቀበሌ ቃለጉባኤ (ናሙና ቀበሌ፡ ጥጥራ ዳሞት) 24

10.4. የጸደቀ የወረዳ ቃለ ጉባኤ (ናሙና ወረዳ: ላይ ጋይንት) 26

1.መግቢያ

1.1. አጠቃላይ ሁኔታ

ከሰሃራ በታች ከ3200 ሜትር ከፍታ በላይ ከሚገኙ አጠቃላይ ውርጭና ውርጭ ቀመስ ሥርዓተ ምህዳሮች (Afroalpine and Sub-afroalpine Ecosystems) /11887 ካ.ኪ.ሜ/ ውስጥ ኢትዮጵያ 73% (8677 ካ.ኪ.ሜ) የሚሆነውን ድርሻ ይዛ ትገኛለች። ከዚህም ውስጥ 83% (7220 ካ.ኪ.ሜ) የሚሆነው የሚገኘው በሀገሪቱ በሚገኙ 9 የተራራ ሰንሰለቶች ነው። በውርጭና ውርጭ ቀመስ ሥርዓተ ምህዳሮች (Afroalpine and sub-afroalpine Ecosystems) ከሚታወቁት 9 የተራራ ሰንሰለቶች ውስጥ ሰባቱ በአማራ ክልል በ6 ዞኖች (በምስራቅ ጎጃም፣ ሰሜን ጎንደር፣ ደቡብ ጎንደር፣ ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ወሎና ሰሜን ሸዋ) የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አምስቱ በሀገራችን ብቻ የሚገኘው የቀይ ቀበሮ መኖሪያ ናቸው።

የጉና ተራራ የቀይ ቀበሮ መጠለያ ከሆኑት አምስት የተራራ ሰንሰለቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን የበርካታ ብዝሐ ህይወት መጠለያና የአባይና ተከዜ አብይ ተፋሰሶች እንዲሁም የጣና ንዑስ ተፋሰስ የውኃ ማማ በመሆኑ ለተፋሰሶች ገባር የሆኑ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች /የ41 ወንዞችና 77 ምንጮች/ መነሻ ነው።

በሀገራችን የሚገኙት የውርጭና ውርጭ ቀመስ ስርዓተ ምህዳሮች የብዝሐ ህይወት ክምችት ቁልፍ ቦታዎች ከመሆናቸውም ባሻገር የምስራቅ አፍሪካ የውኃ ማማዎች ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህ ስርዓተ ምህዳሮች (ውርጭና ውርጭ ቀመስ) በእርሻ መስፋፋት፣ በህገ ወጥ መንደር ምስረታ፣ በልቅ ግጦሽ እና ደን ጭፍጨፋ ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰባቸው ይገኛል።

በተለይም በከፍተኛ ተጽእኖ ውስጥ የሚገኘውና ምንም ዓይነት የአጠቃቀምና አጠባበቅ ስርዓት የሌለውን የጉና ተራራና አካባቢውን ከጥፋት ለመታደግ እንዲሁም የአካባቢውን ማኅበረሰብ በዘላቂነት ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲቻል ቢሮው ከአመልድ/አማራ መልሶ ማቋቋምና ልማት ድርጅት/ ጋር በመቀናጀት በ2005 ዓ.ም መሰረታዊ የብዝሐ ህይወትና ማኅበረ ኢኮኖሚ የዳሰሳ ጥናትና አሳታፊ የእምብርት ዞን ዳር ድንበር ክለላ አካሄዷል። በተጨማሪም ከጥናትና ክለላ ሪፖርቶች በመነሳት ረቂቅ ደንብ አዘጋጅቶ የባለድርሻ አካላትና የማኅበረሰቡ ተወካዮች በተገኙበት አውደ ጥናት በደብረ ታቦር ከተማ በማካሄድ የተሰጡትን አስተያየቶችን በማካተት

ረቂቅ ደንቡን ለማበልጸግ ተሞክሯል ። ስለሆነም አሳታፊ የዳር ድንበር ክለላ የተከናወነለትን የእምብርት ዞን በህግ ለመደገፍና የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራውን በዘላቂነት ጥበቃና አጠቃቀሙን የሚከታተል አካል ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ ለውሳኔ ሰጭ አካላት እንዲረዳ ይህ ደጋፊ ሰነድ ተዘጋጅቷል።

2.የደጋፊ ሰነዱ ዓላማዎች

2.1. አጠቃላይ ዓላማ

በጉና ተራራ ታሳቢ የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ እስከአሁን የተጠኑ ጥናቶችንና የእምብርት ዞን ዳር ድንበር ክለላን መነሻ በማድረግ በታሳቢ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ያለውን ሃብት በዘላቂነት መጠበቅ እንዲቻል ቦታው የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራነት ደረጃ የሚያገኝበትን ህጋዊ እውቅና ለማሰጠት አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተንና ማደራጀት።

2.2.ዝርዝር ዓላማዎች

- የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራውን ዋና ዋና የዱር እንስሳትና ዕጽዋት ሃብት፣ የመሬት አቀማመጥ፣ የአየር ንብረት መረጃ አጠቃሎ ለማቅረብ፣
- ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮሎጂያዊ ሁኔታዎችን ከአሁን በፊት የተካሄዱ ጥናቶችን መነሻ በማድረግ ለማደራጀት፣
- የተጠቃለለውን አሳታፊ የእምብርት ዞን የዳር ድንበር ክለላ ሪፖርትና የአካባቢው ማኅበረሰብና ባለድርሻ አካላት የተስማሙበትን ረቂቅ ደንብ በግብዓትነት በመጠቀም አደራጅቶ ለውሳኔ ሰጭ አካላት ማመቻቸት፣

3.የአየር ንብረትና መገኛ

3.1.መገኛና ስፋት

የጉና ተራራ ውርጭና ውርጭ ቀመስ ስርዓተ ምህዳር በደቡብ ጎንደር ዞን ከደብረ-ታቦር ከተማ ደቡብ ምስራቅ 30 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን አካባቢው በዋናነት በምዕራብና በሰሜን ከፋርጣ ወረዳ፣ በምስራቅና ደቡብ ምስራቅ ከላይ ጋይንት ወረዳ፣ በምዕራብና ደቡብ ምዕራብ ደግሞ ከእስቴ ወረዳ ጋር ይዋሰናል።

በአጠቃላይ ከ11 የገጠር ቀበሌዎች (ላይጋይንት 4 ቀበሌዎች፣ እስቴ 4 ቀበሌዎች፣ፋርጣ 3 ቀበሌዎች) ጋር ይዋሰናል፡፡ የታሳቢ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው እምብርት ዞን በግምት በ$38^0$10’19.59” እና $38^0$16’34.63” ሰሜን ኬክሮስ እና $11^0$39’48.09” እና $11^0$45’31.61” ምስራቅ ኬንትሮስ ላይ የሚገኝ ሲሆን ከባህር ወለል በላይ ያለው ከፍታም ከ3441 እስከ 4113 ሜትር እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ የእምብርት ዞኑ ጠቅላላ ስፋትም 4615 ሄ/ር እንደሚደርስ በአካባቢው የተደረገው የክለላ ሪፖርት ያመላክታል፡፡

የጉና አካባቢ ከደብረ ታቦር በጋሳይ ስማዳ የሚሄደው አንደኛ ደረጃ የጠጠር መኪና መንገድ እና ከነፋስ መውጫ ሳሊ መገንጠያ ስማዳ የሚያገናኘው መንገድ የሚያቋርጠው በመሆኑ ጉናን ለመጎብኘት መንገድ ችግር አይሆንም፤ በተለይም ከደብረ ታቦር በጋሳይ ስማዳ ያለው የጠጠር መንገድ የአካባቢውን ከፍተኛ ቦታዎች አቋርጦ ስለሚሄድ ቦታውን ለመጎብኘት እንደ አንድ እድል ሊወሰድ ይችላል፡፡

3.2.አግሮ ኢኮሎጂና የአየር ንብረት፣

የጉናና አካባቢው የውርጭና ውርጭ ቀመስ ስርዓተ ምህዳሮችን የሚወክል ሲሆን በአካባቢው የሜትሮሎጂ ጣቢያ ባለመኖሩ ምክንያት በትክክል የተወሰደ የዝናብና የሙቀት መጠን መረጃ ባይኖርም ከአካባቢው የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አካባቢው ሁለት የዝናብ ወቅቶች አሉት፡፡ ከፍተኛው የዝናብ ወቅት በክረምት ከሰኔ እስከ መስከረም ሲሆን ዝቅተኛው የዝናብ ወቅት ደግሞ ከመጋቢት እስከ ግንቦት ያገኛል፡፡ ይሁን እንጂ አማካይ የዝናብ መጠን 1068.45 ሚ.ሜ. እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ የአካባቢው ዓመታዊ አማካይ የሙቀት መጠንን በተመለከተ ደግሞ በቅርብ ርቀት በሚገኙት ከተሞች ደ/ታቦር ላይ 15.6°C እና 13°C ነፋስ መውጫ ሲሆን የእምብርት ዞኑ አናት በክረምት ወቅት በበረዶ ይሸፈናል በዚህም ምክንያት የበረዶ መፍያው በመባል ይታወቃል፡፡

4.ብዝሐ ህይወትና ብርቅይነት

ቢሮው ከአመልድ ጋር በመቀናጀት በ2005 ዓ.ም. ባደረገው የዳሰሳ ጥናት መሰረት በጉናና አካባቢው የሚገኘውን ብዝሐ ህይወትና ብርቅይነት በሚመለከት እንደሚከተለው ያብራራዋል፡፡

4.1. አጥቢ እንስሳት

የውርጭና ውርጭ ቀመስ ስርዓተ ምህዳር አካል በሆኑት የጉና ተራራ ሰንሰለቶች የሚኖሩ 30 የተለያዩ የአጥቢ ዝርያዎች የተለዩ ሲሆን ይህም በየብስ ከሚኖሩትና በኢትዮጵያ ከሚገኙት ውስጥ 11% ዝርያዎችን የያዘ መሆኑን ያረጋግጥልናል፡፡

በተጨማሪም በኢትዮጵያና ኤርትራ ብቻ ከሚገኙት 31 የአጥቢ እንስሳት ዝርያዎች ውስጥ 6ቱ ብርቅየ ዝርያዎች (19% የሚሆኑት) በቦታው ይገኛሉ፡፡ በተለይም በሀገራችን ብቻ ከሚገኙ ከታላላቅ አጥቢዎች መካከልም ህልውናቸው በእንክብካቤ ላይ ከተመሰረቱት (Conservation Dependant) ውስጥ የጭላዳ ዝንጀሮ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለእልቂት የተቃረበው (Globally Endangered) ቀይ ቀበሮ ይገኙበታል፡፡

4.2. አእዋፋት

በአገራችን ከሚገኙ 864 የአእዋፋት ዝርያዎች ውስጥ 139 (16%) አእዋፋት በዚህ አካባቢ የተለዩ ሲሆን፣ በሀገራችን ብቻ ከሚገኙት 18 ብርቅየ የአእዋፋት ዝርያዎች ውስጥ 5ቱ /28%/ እና ሀገራችን ከኤርትራ ጋር ከምትጋራቸው 13 ብርቅየዎች ውስጥም 8ቱ በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ ናቸው፡፡

በተጨማሪም የዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ማኅበር /IUCN/ በአዘጋጀው ቀይ የዝርዝር መዝገብ /Red Data Book/ መሰረት በኢትዮጵያ 36 አእዋፋት ዝርያዎች በእልቂት ስጋት ደረጃ ያሉ ሲሆን እነዚህም 2 ለእልቂት የተቃረቡ/Endangered/፣14 ለእልቂት የሚያበቁ ሁኔታዎች ካልተገደቡ ለእልቂት ከተቃረቡት ምድብ የሚሸጋገሩ/Vulnerable/፣16 ለእልቂት ስጋት የተቃረቡ/ Near Threatened/ና 4 የመረጃ አጥረት ያለበት/Data Deficient/ ናቸው፡፡ ከዚህም ውስጥ በጉናና አካባቢው 5 (13.9% ከሀገሪቱ) አእዋፋት ዝርያዎች በእልቂት ስጋት ደረጃ ያሉ ሲሆን እነዚህም፡-

- 1 ለእልቂት የተቃረበ/Endangered/፣
    - Ankober serin (*Serinus ankoberensis*)
- 1 ለእልቂት የሚያበቁ/የሚያደርሱ ሁኔታዎች ካልተገደቡ ለእልቂት ከተቃረቡት ምድብ የሚሸጋገሩ/Vulnerable/፣
    - Great spotted eagle (*Aquila clanga*)

- 3 ለእልቂት ስጋት የተቃረቡ/Near Threatened/
    - Abyssinian longclaw (*Macronyx flavicollis*)
    - Blue-winged goose (*Cyanochen cyanopterus*)
    - White collared pigeon (*Columba albitorques*)

4.3. የእፅዋት ሽፋንና ዓይነት

የጉና ተራራ ሰንሰለትና አካባቢው ከ96 በላይ የሚሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎችን የያዘ የተፈጥሮ አካባቢ ነው፡፡ ይህ አካባቢ በዋናነት የውርጭና ውርጭ ቀመስ ስርዓተ ምህዳሮችን ተከትሎ የአስታ፣ ጀበራ፣ የዋልያ እሾህ፣ ጓሳ፣ ጭማ፣ አምጃ፣ ኮሶ፣ ቀጋና አሸንዳ ዕፅዋትን አቅፎ የያዘ ሲሆን በደረቅ ተራራዎች ደንና ቅጠላቸው የማይረግፍ ቁጥቋጦዎች (Dry Evergreen Montane Forest Ecosystem) ሥርዓተ ምህዳር ደግሞ ቅጠላቸው ከማይረግፉ የዛፍና ቁጥቋጦ ዝርያዎች መካከል እንደ የሀበሻ ጽድ፣ ወይራ፣ ኮሶ፣ ክትክታ፣ ደደሆንና ሌሎች ዝርያዎችን ያካትታል፡፡

የጉና ተራራ ሰንሰለትና አካባቢው ከላይ በተጠቀሱት ሥርዓተ ምህዳሮች ብዛት ያላቸው ለመጥፋት የተቃረቡና ዝርያቸው በመመናመን ላይ የሚገኙ ሀገር በቀል ዛፎችን የያዘ ከመሆኑም በላይ በተለይም በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ 5 ዝርያዎችን፡-

- *Acanthus sennii* /ኮሸሸላ/
- *Echinops ellenbeckii*/ጓሌ/
- *Kniphofia foliosa*/አሸንዳ/
- *Lobelia rhynchopetalum*/ጅብራ/ጀበራ/
- Helichrysum hochstetteri/ነጭሎ/

የያዘ ስለሆነ አካባቢው የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ለጥፋት ተጋላጭ የሆነውን የውርጭና ውርጭ ቀመስ ስርዓተ ምህዳር ማልማትና መንከባከብ ያስፈልጋል፡፡

5. በተፈጥሮ ሃብቱ አካባቢ ያሉ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ኃይማኖታዊ የቱሪዝም ሃብቶች ሁኔታ

በጉና ተራራ ዙሪያ የሚገኙ ኃይማኖታዊና ታሪካዊ ቅርሶች በታሳቢ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ካሉ የተፈጥሮ ሃብቶች እንዲሁም ከቦታው ማራኪ ገጽታ ጋር በማስተሳሰር ወደ ልማት ገብተው የቱሪስት መዳረሻ መሆን ቢችሉ በሚኖረው የቱሪዝም እንቅስቃሴ ምክንያት ለክልሉም

ሆነ ለአካባቢው ማኅበረሰብ ከፍተኛ የሆነ የማኅበረ ኢኮኖሚ አስተዋጸ ማበርከት ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ ቅርሶች ውስጥ በከፊል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡-

- **ጋፋት**: ከደብረ ታቦር ከተማ ሰሜን ምስራቅ 4.4 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ይህ ቦታ በተለይም ከአጼ ቴዎድሮስ 2ኛ የጀግንነት ታሪክ መነሻና መድረሻ ጋር ሰለሚተሳሰር ቱሪስትን ለመሳብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ በአሁኑ ስዓትም የሴባስቶፖል መድፍን ለመስራት ይጠቀሙበት የነበረው ማቅለጫ ጉድጓድ፣ የእንግሊዝ ጠቢባን መኖሪያ የነበሩ ቤቶች ፍርስራሽና የአጼ ታዎድሮስ የፈረስ ማሰሪያ የነበሩ ቦታዎች ከነችግራቸውም ቢሆን ለጎብኝዎች በግልጽ መታየት የሚችሉ ቦታዎች ናቸው፡፡

- **የሰመርናሃ ቤተመንግስት**: ከደብረ ታቦር ከተማ ሰሜን ምስራቅ 9 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ይህ ቤተመንግስት በአጼ ዮሐንስ 4ኛ በ1872 ዓ.ም ተገንብቶ በውስጡም የቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን አብሮ ተተክሎበታል፡፡
- **ዙር አባ አቡነ አረጋዊ ገዳምና የዝማሬ፣ መስዋት ማስመስከሪያ ዩኒቨርሲቲ**: ከወረታ ወልድያ የሚወስደውን የአስፓልት መንገድ ተከትሎ ከደብረ ታቦር ከተማ 55 ኪ.ሜ እና ከነፋስ መውጫ ከተማ ደግሞ 25 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ከምተገኘው ሳሊ ከተማ 6 ኪ.. ሜ ገባ ብሎ በስተደ/ምዕራብ አቅጣጫ ይገኛል፡፡ የዙር አባ ጽርሃ አርያም አቡነ አረጋዊ ገዳም በ533 ዓ.ም በቅዱስ ያሬድ፣ አቡነ አረጋዊና በአጼ ገብረ መስቀል አማካኝነት አንደተመሰረተና የጉና ተራራ ስያሜም ከገዳሙ መስራቾች ንግግር ጋር የተያያዘ እንደሆነ በገዳሙ የሚገኙ ልዩ ልዩ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ በገዳሙ ውስጥ ጥንታዊያን የብራና መጻሕፍት፣ የግድግዳ ላይ ስዕላትና ልዩ ልዩ ንዋያተ ቀድሳት እና ከቀደምት ነገስታት ለገዳሙ በስጦታ የተበረከቱ ዘውዶች፣ ጋሻዎችና አልባሳት የጥንት ስልጣኔዎችን እየገለጹ ይገኛሉ፡፡ ገዳሙ ከቦታው አቀማመጥ ማራኪነት በተጨማሪ ከ15000 ዓመታት በላይ የዝማሬና መዋስት ማስመስከሪያ ዩኒቨርሲቲ በመሆን ስለሚያገለግል ከሃገራችን የተለያዩ ቦታዎች የመጡ በርካታ ወጣት ምሁራን ይገኛሉ፡፡
- **ውቅሮ መድኃኔዓለም ውቅር ቤተክርስቲያን**: በወረታ ወልድያ የሚወስደውን አስፓልት መንገድ ተከትሎ በመሄድ ከክምር ድንጋይ ከተማ 4 ኪ.ሜ ሰሜን አቅጣጫ ላይ የሚገኝ ሲሆን ቤተክርስቲያኑ በቅዱስ ላሊበላ ተጀምሮ በአቡነ መልከጼዴቅ አንደተጠናቀቀ የገዳሙ ታሪክ ያስረዳል፡ አሰራሩም አጅግ ማራኪና በውስጡም ልዩ ልዩ የኪነ ህንጻ ጥበብ ያረፈባቸው በርካታ ክፍሎችን፣ የቅዱሳን አጽሞችና የጥንት ብራና መጻሕፍት ይገኛሉ፡፡

- **ቅድስት ቤተልሔም**: ከታች ጋይንት ወረዳ ከተማ አርብ ገበያ 34 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የምትገኝ ሲሆን በ4ኛው ክ/ዘመን በአብርሃ ወአጽብሓ አንደተመሰረተችና ከአጼ ሰርጸድንግል የንግስና ዘመን ጀምሮ ደግሞ ብቸኛዋ የድጓ ማስመስከሪያ ዩኒቨርሲቲ በመሆን እንዳገለገለች የገዳሙ ታሪክ ያስረዳል፡፡ የቤተክርስቲያኑ የውስጥ የአሰራር ጥበብ፣ በውስጡ የሚገኙ በርካታ የጥንት የብራና መጻሕፍትና ስዕላት እንዲሁም የተማሪዎች መኖሪያ የሳር ጎጆዎች የቱሪስትን ቀልብ በቀላሉ መሳብ የሚችሉ ሃብቶች ናቸው፡፡

6. በታሳቢ የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የሚኖሩ ህዝቦች አኗኗርና የሚያደርሱት ተፅዕኖ

6.1. የአካባቢው ነዋሪዎች ሁኔታ

በ2002 ዓ.ም አገር አቀፍ የህዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት መሰረት፣ በአሁኑ ወቅት የጉና ታሳቢ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ አዋሳኝ በሆኑት 11 ቀበሌዎች ከ 78,804 ያላነሰ ህዝብ (40,646 ወንድና 38,158 ሴቶች) ይኖራሉ፡፡ ይህ ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ቦታ በሚያካልላቸው ቀበሌዎች በ2002 ዓ.ም ላይ የነበረው የሰው ጫና ከ275.2 እስከ 171.65 ሰው/ካሬ ኪ.ሜ ይደርሳል፡፡

እንደ ሌሎች የኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታ አርሶ አደሮች በጉና ታሳቢ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ አካባቢዎች ለሚኖረው ህብረተሰብ የሰብል እርሻና የቤት እንስሳት እርባታ ዋነኛ መተዳደሪያው ነው፡፡ በመሆኑም በአካባቢው የሚገኘው ውርጭና ውርጭ ቀመስ ስርዓተ ምህዳር ለእርሻ፣ ለቤት እንስሳት ግጦሽ፣ ለማገዶና ለኮንስትራክሽን እንጨት ፍጆታ ወዘተ በማገልገል ለማህበረ ኢኮኖሚው በቀጥታና በተዘዋዋሪ ከፍተኛ ጠቀሜታዎችን ይሰጣል፡፡ በአካባቢው ገብስ፤ ድንች፣ ስንዴና ባቄላ አንደ ቅደም ተከተላቸው ተመራጭ ሆነው የሚመረቱ ሰብሎች ናቸው፡፡

ከሰብል አዝመራው ጎን ለጎን በጉና ተራራ ዙሪያ የሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል የሚከውነው የቤት እንስሳት እርባታ፣ ለየቤተሰቡ የእርሻ ስራ፣ ለሰውና እቃ ማጓጓዣ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመሄድ ላይ ካለው የስጋ ገበያ ገቢ ለማግኘት እያገለገለ ነው፡፡

በእነዚህ ምክንያቶች የአካባቢው ነዋሪ የቀንድ ከብት፣ በግና የጋማ ከብት በልቅ ግጦሽ እያረባ ይኖራል፡፡ በመስክ ስራ ወቅት ለአንዳንድ ነዋሪዎች ከቀረበው መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ቃለ መጠይቅ በተገኘው ምላሽ፣ በአካባቢው በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ባለ አንድ ቤተሰብ በአማካይ

ቢያንስ 6 በግ እና 2 የጋማ ከብት (ፈረስ/ በቅሎ) የሚኖረው ሲሆን በከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ባለ አንድ ቤተሰብ ደግሞ በአማካይ ቢያንስ 1 በሬ፣ 2 ላሞች፣2 ፈረሶች፣ 2 በቅሎዎች፣ እስከ 15 በጎች ይኖረዋል፡፡ ከዚህ መረጃና ከየወረዳው ግብርና ጽ/ቤት ከተሰበሰበው መረጃ በመነሳት፣ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አካባቢ ለሚገኘው ነዋሪ በግ ማርባት ቀዳሚ ምርጫ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም፣ ከተፈጥሮ ሀብቱ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ በመሄድ ላይ ያለው ህዝብ ቁጥርና ሃብቱን የመጠቀም ፍላጎት ሀብቱን ጠብቆ ለማቆየት በሚደረጉ ጥረቶች መካከል ጉልህ የሆነ የአለመጠጣም ችግሮች አንዳሉ ከዚህ በፊት የተካሄደው የጥናት ውጤት ያረጋግጣል፡፡

6.2. በተፈጥሮ አካባቢው ላይ የሚታዩ ጫናዎች/ተጽዕኖዎች

በጉናና አካባቢው የሚኖረው ህዝብና የቤት እንስሳት ቁጥርና ጫና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ ሳቢያ ለከፍተኛ የአፈር ክለት ተጋላጭ የሆኑት የውርጭና ውርጭ ቀመስ ስርዓተ ምህዳሮች በከፍተኛ ተጽእኖ ውሰጥ የሚገኙ ሲሆን በጥብቅ ስፍራው ከሚታዩት ዋና ዋና ችግሮች መካከልም፡-

- **ሰፊ የሆነ ልቅ ግጦሽ መኖር፡-** የአካባቢው ማኅበረሰብ ሙሉ በሙሉ በልቅ ግጦሽ እርባታ ሥርዓት የተቃኘ ልማድ ስላላቸው በጥናቱና ክለላው ወቅት እንደተረጋገጠው በጥብቅ ስፍራው ውስጥ የቤት እንስሳት የማይደርሱበት ቦታ የለም፡፡
- **የደን ጭፍጨፋ፡-** በአካባቢው ከልቅ ግጦሽ ጫና ጋር የደን ምንጣሮና ቃጠሎ በስፋት ስለሚከናወን ውጤቱም የአካባቢውን የውኃ ማማነት ከማስጠበቅ ይልቅ ከፍተኛ ቦረቦሮችን ፈጥሯል፡፡
- **ህገወጥ እርሻና የሰፈራ መስፋፋት፡-** በደርግ ውድቀት ዋዜማ የተጀመረው የመንደር ምስረታ እየተስፋፋ ከታች የሚኖረው ኅብረተሰብ ወደ ተራራው አናት በመውጣት በአሁኑ ስዓት ለሰው ልጅ መኖሪያ ተስማሚ ባልሆኑ ቦታዎች እስከ 3700 ሜትር ከባህር ወለል በላይ መንደሮች ይገኛሉ፡፡
- **የእርሻ መስፋፋት** ፡- በኢትዮጵያ በሚገኙ ከፍተኛ ቦታዎች በየዓመቱ ከ1.9 አስከ 3.5 ቢሊዮን ቶን የላይኛውና ለም የሆነው አፈር እንደሚታጠብ ጥናቶች የሚያሳዩ ሲሆን በዚህ ሳቢያም ወደ 10 ሚሊዮን የሚጠጉ አርሶ አደሮች የእርሻ መሬታቸው ከጥቅም ውጭ

ይሆናል (EFAP, 1993; EHRS, 1984)። የዚህ አይነት ችግር ሰለባ የሆነው የጉና ታሳቢ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ከፍተኛ የሆነ የእርሻ መሬት መስፋፋት በወረራ መልኩ እስከ 3800 ሜትር ከባህር ወለል በላይ ድረስ እየተካሄደ የሚገኝ ሲሆን በተለይም በእስቱ ወረዳ ዕለት ድባና ቀበሌና በላይ ጋይንት ወረዳ ጉና ገደባ ቀበሌ በኩል ችግሩ ገዝፎ ይገኛል።

- **የወኃ ሃብት ብክነት/water resources degradation/፡-** የጉና ታሳቢ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ የአባይና ተከዜ አብይ ተፋሰሶች እንዲሁም የጣና ተፋሰስ የውኃ ማማ በመሆኑ ለተፋሰሶች ገባር የሆኑ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች /የ41 ወንዞችና 77 ምንጮች/ መነሻ ነው። ይሁን እንጂ ከላይ በተጠቀሱት እርስ በርሳቸው የተሰናሰሉ ችግሮች ድምር ውጤት ምክንያት በአካባቢው የሚዘንበው ዝናብ ወደ መሬት መስረግ ባለመቻሉ
    - በታችኛው የተፋሰስ ክልል ጎርፍን አባብሷል፣
    - የወንዞች ፍሰት ዓመቱን ሙሉ ከመሆን ይልቅ ወቅታዊ እንዲሆን አድርጓል፣
    - በታችኛው አካባቢ የውኃ አቅርቦት እጥረት በመፈጠሩ ምክንያት የመጠጥ ውኃ ችግር ተከስቷል፣
    - በታችኛው አካባቢ ደለል በዝቷል፣
    - የአየር መዛባትን ተከትሎ ድርቅን እያስፋፋ ነው፣
    - በጣና ሐይቅና በታችኛው ተፋሰስ አካባቢ የሚገኙ ወንዞች ለጎርፍና ደለል መሞላት መንስኤ ሆኗል፣

በመሆኑም የጉና አካባቢን መጠበቅ ለብዝሃ-ህይወት ጥበቃ ብቻ ሳይሆን የብዙ ወንዞች መነሻ በመሆኑ ይህን አካባቢ ከጉዳት መከላከል የአካባቢውን ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆን የታችኛውን ተፋሰስ የውሃ ተጠቃሚ ለማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ረጅም ጊዜ ሳይወስድ ህጋዊ ዕውቅና እንዲያገኝ ማስቻል ለነገ የማይባል ተግባር ነው።

7. የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የሚኖረው ጠቀሜታ

ሀ/ ሥነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ

- *ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር ያላቸዉ ግብግብ ዘለቄታዊ የተፈጥሮ ገጽታ መኖርን ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ እንዲሆን ማድረግ ያስችላል። በዚህም ዘለቄታዊ ጥቅም አለዉ*
- *በአካባቢው ያለው ስርዓተ ምህዳር እንዳይዛባ ከፍተኛ አስተዋፆ ያደርጋል ።*

- *ለክለት ተጋላጭ የሆነው የከፍተኛ ቦታዎች ሰነምህዳር ለመጠበቅ ያስችላል፡፡*
- በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ ያለው ብዝሃ ህይወት ሳይጠፋ እንዲኖር፡ያስችላል
- በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በአይነትም ሆነ በብዛት ይጠበቃሉ፣
- የዱር እንስሳትና ዕፅዋት በቦታቸው እንዲጠበቁና እንዳይጠፉ ይረዳል፣
- የተስተካከለ የውሃ ሃብት እንዲኖር ያስችላል (ከማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የሚነሱ ምንጮችና ጂረቶች ዓመቱን በሙሉ እንዲፈሱ ያስችላል)፡፡

ለ/ ኢኮኖሚያው ጠቀሜታ

- በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ከጐብኝዎች ጋር ተያይዞ ከቱሪዝም አማራጭ ገቢዎች ለህብረተሰቡና ለመንግስት ገቢ ያስገኛል፣
- ከምርምርና ሣይንሳዊ ጥናት እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የአካባቢውን ገቢና አቅም ያጐለብታል፣
- የኢኮ-ቱሪዝም እንቅስቃሴ ስለሚስፋፋ ለአካባቢው ህብረተሰብ አንድ የገቢ ምንጭ ይሆናል፡፡
- የአካባቢው የአየር ሚዛን ስለሚጠበቅ ከእርሻ ስራ የሚገኘው ገቢ ዘላቂና አስተማማኝ ይሆናል፡፡
- በሆቴልና አገልግሎት በመስጠት በርካታ ነዋሪዎች ኑሯቸዉን ማሻሻል ይችላሉ ተጨማሪ እዉቀትም ይኖራቸዋል፡፡

ሐ/ ማህበራዊ ጠቀሜታ

- ዓለማቀፋዊና ማህበረሰባዊ የሆኑ ጠቃሚ የባህልና ልምድ ልውውጥ ይኖራል፣
- በአካባቢው የሚገኙ ነዋሪዎች የተፈጥሮ ቦታውን ለመጠበቅም ሆነ በአገባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ዘላቂ የሆነ የጓሳ አጠቃቀም እንዲኖር ያስችላል፡፡

መ/ ሳይንሳዊ ጠቀሜታ

- የዱር እንሰሳትና ዕፅዋትን ባሉበት ሁኔታና በተፈጥሮአዊ አኗኗራቸው ለሚደረግ ምርምር በማእከልነት ያገለግላል፡፡

- የባህላዊ መድሃኒቶችን ደህንነት በመጠበቅና በመንከባከብ ጥቅም ላይ በማዋል ሣይንሳዊ ጥናትንም ለማካሄድ ይረዳል፡፡
- በመጥፋት ላይ ላሉ የዱር እንስሳትና እጽዋት ሳይንሳዊ ምርምር ሊድረግ ያስችላል፡፡
- በጓሳውና ገጽታዉ ለከባቢያዊ ደህንነት፤ ለብዝሃ ህይወትና ለስርዓተ ምህዳር መስተካከል ያላቸው አስተዋጽዖ ይታወቃል በዚህ ረገድ ለሚደረጉ ምርምሮች የመስክ ላቦራቶር ሊሆን ይችላል፡፡

መ/ የተፈጥሯዊነት ጠቀሜታ

- ተፈጥሯዊነትን ጠብቆ ለመቆየት ያስችላል፡፡ በውስጡ ያሉትን ብዝሃ ህይወትና ሌሎች (አፈር፤ዉሃና የመሬት አቀማማጥ) በተፈጥሮአዊ ገጽታቸው ቆይተው ዘለቄታ ባለው መልክ ጥቅም እነዲሰጡና ተፈጥሮአዊ ይዘታቸው እንዳይጓደል ይረዳል፡፡

ሠ/ የመስህብነት ጠቀሜታ

- አካባቢው የሰው ልጅን ቀልብ ሊገዙ የሚችሉ ማራኪ ገጽታወች የያዘ ከመሆኑም በተጨማሪ ቀይ ቀበሮን ቁርስ እበሉ ሊያዩበት የሚችል በመሆኑና በብዙ ተፈጥሯዊና ባህላዊ ቅርሶች ተከበበ ስለሆነ የመስህብነት ጠቀሜታውን የጎላ ያደርገዋል፡፡

ስለሆነም ይህ የበርካታ ብዝሐ ህይወት መጠለያና የምስራቅ አፍሪካ የውኃ ማማ የሆነ አካባቢ በማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ አጠባበቅ ሥርዓት መሰረት ዘላቂ በሆነ ጥበቃና አጠቃቀም ተጠብቆ ለትውልድ እንዲተላለፍ በጥብቅ ስፍራነት ተከልሎ የሚያበረክተው አኮኖሚያዊ፣ ስነምህዳራዊ፣ ሳይንሳዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታውና ዓለማቀፋዊ አስተዋጾው ከፍ ማለት እንዳለበት ያሳያል፡፡

8. የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው የወደፊት የጥበቃ ሁኔታ

የጉና ተራራ ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ አስከአሁን ድረስ ምንም አይነት ጥበቃ ስለማይደረግለት በእልቂት ስጋት ላይ ያለ አካባቢ ስለሆነ ለወደፊት አስተዳደሩን በተመለከተ ተጠሪነቱ ለክልሉ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮና ለጓሳ ተጠቃሚው ማህበረሰብ የጓሳ ልማትና ጥበቃ ም/ቤት የሆነ ጽ/ቤት ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡ የጥበቃ ስራውም በመንግስት በሚቀጠሩ የመንግስት ስካውቶችና በማህበረሰቡ በሚመረጡ የማህበረሰብ ስካውቶች የጥበቃ

ስራው ይካሄዳል፡፡ የጥብቅ ስፍራውን ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመሆን ለማልማትና ለመጠበቅ የሚቋቋመው ተቋም ለስራው አመች በሆነ ቦታ ይቋቋማል፡፡ የሚቋቋመው ጽ/ቤትም በማህበረሰብ ጥብቅ የስፍራው ውስጥ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

- የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራውን የሚጠብቁ የአካባቢ የደን ጥበቃ ስፍራዎችን መቆጣጠር፣
- ከጎብኝዎች ሚሰበሰብ ገንዘብን ለአካባቢው ሕብረተሰብ ልማት በአግባቡ ሚውልበትን ሁኔታ ይከታተላል፣
- የጓሳውን መዝጊያና መክፈቻ ጊዜ የቆጣጠራል ያስከብራል (ለሁለት ዓመት ከአስር ወራት ከተዘጋ በኋላ ለሁለት ወራት ክፍት ይሆናል)፣
- ከቤትእንስሳት ወደ ዱር እንስሳት የሚተላለፉ የእንስሳት በሽታዎች ላይ ቁጥጥር ያደርጋል፣
- የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራውን በተመለከተ የአካባቢውን ማህበረሰብ በማስተባበር የልማት ስራዎችን ያከናውናል፣
- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ የዱር እንስሳት ቁጥጥርና ጥበቃ እንዲካሄድ ያደርጋል፣

9. ማጠቃለያ

በከፍተኛ ተጽእኖ ውስጥ የሚገኘውና ምንም ዓይነት የአጠቃቀምና አጠባበቅ ስርዓት የሌለውን የጉና ተራራና አካባቢውን ከጥፋት ለመታደግ እንዲሁም የአካባቢውን ማኅበረሰብ በዘላቂነት ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲቻል ቢሮው ከአመልድ/አማራ መልሶ ማቋቋምና ልማት ድርጅት/ ጋር በመቀናጀት በ2005 ዓ.ም፡-

- በጉና ተራራ አካባቢ የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራ የመሆን አቅም መሰረታዊ የብዝሐ ህይወትና ማኅበረ ኢኮኖሚ የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፣
- ከአዋሳኝ ቀበሌዎች ከ60 በላይ አርሶ አደሮችን በመውሰድ በመንዝ ጓሳ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ልምድና ተሞክሮ እንዲያገኙ ተደርጓል፣
- የጉና እና አካባቢውን ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ለማድረግ የሚያግዝ ትልቅ የምክክር አወደ ጥናት ከአመልድ ጋር በመተባበር በደብረታቦር ከተማ 137 ያህል የአካባቢው አርሶ አደሮች የተሳተፉበት አውደ ጥናት ተካሂዷል፡፡ የአውደ ጥናቱ ዓላማ ጉናን ለመከለል የሚቻልበትን ስልት ለመንደፍ፣ ህዝቡን ለማሳመንና ይህን ስራ የሚያስተባብር ግብረ ኃይል ለማቋቋም ነበር፡፡ በዙኑ ዋና አስተዳዳሪ የሚመራ የአካባቢ ጥ/መ/አ/አ/መምሪያ፣ የባህልና

ቱሪዝም መምሪያ፣ የአስተዳደርና ፀጥታ ያሉበት ግብረ ኃይል የማቋቋም ስራና አደረጃጀቱን ወደ ወረዳ የማውረድ ስራም ተሰርቷል፣

- በዞን ደረጃ የተቋቋመው ግብረ ኃይል የጉናን አካባቢ ለመከለልና ወደ ጥብቅ ስፍራነት ለማምጣት የሚያስችል የድርጊት መርሐ ግብር በማዘጋጀት ለወረዳዎች በመላክ ድጋፍና ክትትል ያደረገ ሲሆን ከዚህ በመነሳት ወረዳዎችም የራሳቸውን የአፈጻጸም መርሐ ግብር አዘጋጅተዋል፡፡ በመርሐ ግብሩ መሰረትም ከሚመለከታቸው የወረዳ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የተውጣጡ አካላት ወደ አጎራባች ቀበሌዎች በመንቀሳቀስ በመጀመሪያ የቀበሌ አመራሮችን፣ በመቀጠል በየቀበሌው የሚገኙ ግንባር ቀደም አርሶ አደሮችን ከዚያም ከቀበሌው ማኅበረሰብ ጋር በክለላው ዙሪያ ውይይት ተደርጓል፡፡ በውይይቱም የእምብርት ዞኑ መከለል እንዳለበት የጋራ ስምምነት ላይ በመድረስ በክለላው ወቅትም ከባለሙያዎች ጋር የሚሳተፉና የዳር ድንበር ከላይ ኮሚቴ አባላትን ከአካባቢው ማኅበረሰብ ተወካዮን (ሽማግሌዎችን) የመምረጥ ስራ ተሰርቷል፣
- ህብረተሰብ አሳታፊ የእምብርት ዞን ዳር ድንበር ክለላ ተካሄዷል፡፡ በክለላው ወቅትም ወደ 117 የሚደርሱ ከአመራር፣ ከባለሙያዎችና ከአካባቢው ሽማግሌዎች የተውጣጣ ኃይል በስራው ሙሉ ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡ በአጠቃላይ የታሳቢ ማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራውና የቀበሌዎች ወሰን ምልክቶችን የመለየትና የጂፒኤስ ንባቦችን (ከወሰን መለያ ቁጥር 001 እስከ 528) በመውሰድ የተከለለ ሲሆን ከየቀበሌው በተመረጡ የዳር ድንበር ክለላ የኮሚቴ አባላት ስምምነት የተረጋገጠውን ቃለ ጉባኤ ሁሉም ቀበሌዎች ጉዳዩን አምነውበት ስምምነቱን አጽድቀውታል፡፡ የሁሉም አዋሳኝ ቀበሌዎች የዳር ድንበር ወሰን ክለላ ከተጠናቀቀ በኋላ በቀበሌ ደረጃ የጸደቀውን መነሻ በማድረግ የተያዘው ቃለ ጉባኤና የኮሚቴዎችን የስምምነት ፊርማ የወረዳው ካቢኔ ተወያይቶ ከመረመረ በኋላ በወረዳ ደረጃ እንዲጸድቅ ተደርጓል፡፡ በቀበሌና በወረዳ ደረጃ የጸደቀው የዳር ድንበር ወሰን የክለላ ሰነድ አንድ ኮፒ ለየቀበሌው አስተዳደር፣ አንድ ኮፒ ለየወረዳው አስተዳደር፣ አንድ ኮፒ ለየወረዳው አካባቢ ጥ/መ/አ/አ/ ጽ/ቤት፣ ዋናው ኮፒ ደግሞ ለክልሉ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡
- ከጥናትና ክለላ ሪፖርቶች በመነሳት ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ከ200 በላይ የባለድርሻ አካላትና የማኅበረሰቡ ተወካዮች በተገኙበት አውደ ጥናት በደብረ ታቦር ከተማ በማካሄድ የተሰጡትን አስተያየቶችን በማካተት ረቂቅ ደንቡን ለማበልጸግ ጥረት ተደርጓል፣

የጉና ታሳቢ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ጥብቅ ቦታ የመሆን አቅም ባለው የተፈጥሮ አቀማማጥ፤ ብዝሃ ህይዎትና የሚሠጠው ጠቀሜታ የተገለጸ ቢሆንም በጥናቱ እንደተረጋገጠው ወሳኙ ያሉትን ችግሮች በመቅረፍና የተፈጥሮ ሃብቱ ወደ ነበረበት የመመለስ ጥረት ላይ የወደቀ ነው፡፡ ለዚህም ሁሉም አጋር አካላት የየድርሻቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ከሆነ የጉና ታሳቢ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ በመሆን የሚከተሉትን አላማዎች የሚያሳካ ይሆናል፡፡

- ***ለብዝሃ ህይወት ጥበቃ፡*** ባለው ስርዓተ-ምህዳር ውስጥ የብዝሃ ህይወት ሃብትን የዘቦታ/Insitu conservation/ ልማትና ጥበቃ ለማካሄድ የሚያስችል የዕጽዋትና እንሰሳት ስብጥርን በማጥናት፤በማልማትና በመጠበቅ ለተተኪ ትውልደ ለማሰተላላፍ፡፡
- ***ማራኪ የመሬት አቀማመጥንና ተፈጥሮአዊ ገፅታን ለመጠቀምና ለማቆየት፡***-ተፈጥሮአዊና ማረኪ የሆነውን የመሬት አቀማመጥ ለሰው ልጆች አእምሮ ማደሻ በማድረግ የመዝናኛ እድሎችን መፍጠርና በተፈጠሮአዊ ገፅታው በማቆየት በዚህ ሁኔታ በውስጡ ያሉትን ተፈጥሮአዊ ሃብቶች በዘላቂ ቱሪዝምና በተመጣጣኝ አጠቃቀም ጥቅም ላይ ለማዋል፡፡
- ***ለትምህርትና ምርምር፡*** ብዝሃ ሕይወትንና ተፈጥሮአዊ አካባቢዎችን የትምህርትና የምርምር ማዕከል በማድረግ በዘርፉ የሚጠበቀውን ሳይንሳዊ እድገት ለማመጣትና አግባብ ባለው መንገድ ለማልማትና ለመጠቀም፡፡
- ***በዘላቂ ቱሪዝም ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማስፋፋት፡*** የተፈጥሮ መዝናናዎችን በማስፋፋትና በኢኮቱሪዘም በመደራጀት ለጎብኝዎች በሚሠጥ አገልግሎት የነዋሪውን ህዝብ ኑሮ ማሻሻልና መሰረተ ልማቶችን ለማሳደግ፤ በዚህም ዋነኛ የገቢ ምንጭ በመሆን በኢኮኖሚው እድገት ከፍተኛ አስተዋጾ ለማበርከት ያስችላል፡፡
- ***አካባቢው የሚሰጠውን አገልግሎት /Ecosystem services/ በተሸለ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማስቻል፡*** የጉና አካባቢ በክልሉ ለሚገኙት ሁለት አብይ ተፋሰሶች (የአባይና የተከዜ አብይ ተፋሰስ)ና ለጣና ተፋሰስ ገባር የሆኑ ከ41 በላይ ዋና ዋና ወንዞች እና ከ77 በላይ ምንጮች መነሻ በመሆኑ በተፋሰሱ የላይኛው አካልና በታችኛው አካባቢ የሚኖሩ ለመጠጥና ሌሎች አገልግሎቶች ሊውል የሚችል ውኃ ማግኘት የሚያስችል ቦታ ከመሆኑም በተጨማሪ የህዳሴው ግድብ ህልውናም የሚመሰረተው በጉናና መሰል ስርዓተ ምህዳር ባላቸው አካባቢዎች በመሆኑ ጉናን ማልማትና መጠበቅ የህዳሴውን ግድብ ደህንነት መጠበቅ ነው፡፡ ሰለዚህ የጉናን ስርዓተ ምህዳር መጠበቅ የአካባቢውን የአየር ሚዛን ለመጠበቅ ያስችላል፡፡

10. ዕዝል

10.1 የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ወሰን ዝርዝር መግለጫ

የማህበረሰብ ጥብቅ ቦታን አከላለልና አዋሳኝ ሥፍራዎችን በኬክሮስ/ላቲቲዩድ/ እና በኬንትሮስ /ሎንግቲዩድ/ ነጥቦች የሚያሳዬው ዝርዝር መግለጫ ከዚህ በታች ተመልክቷል፡-

1. የማኅበረሰብ ጥብቅ ስፍራውን በደቡብ ምዕራብ አቅጣጭ ከሚያዋስነው ከእስቴና ከፋረጣ ወረዳዎች ደንበር ማለትም ከልዋየና ሶራስ ቀበሌ ደንበር ወፋይ ጎጥ ላይ 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 55.0 ሴኮንድ ሰሜን እና በ38 ዲግሪ 10 ደቂቃ 36.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አንድ መነሻ በማድረግ፣
2. ከዚያም ከልዋየ ቀበሌ ደንበር ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመቀጠል ከጥቁሬ ዱር ማለትም ከልዋይና ውጭባ ቀበሌ ደንበር ላይ 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 45.1 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 10 ደቂቃ 53.1 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሁለት፣
3. ከዚያም የውጭባ ቀበሌ ደንበርን ተከትሎ በዚያው አቅጣጫ በመቀጠል ትምህርት ቤቱን ወደ ውጭ በመተው ጀፍጀፍ ወንዝ ላይ 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 34.4 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 11 ደቂቃ 08.1 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሶስት፣
4. ከዚያም የውጭባ ቀበሌ ደንበርን ተከትሎ ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በመሄድ እርከኑን ወደ ውስጥ በማስገባት በልግ ጥግ ላይ 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 20.3 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 10 ደቂቃ 53.7 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አራት፣
5. ከዚያም የእርከኑን ደንበር ተከትሎ ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመሄድ በልግ ጥግ አካባቢ ደረቅ ወንዝ መነሻ ላይ 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 03.6 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 10 ደቂቃ 49.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምስት፣
6. ከዚያም የሞሰቢት ተራራ ወደ ውስጥ በማድረግ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመጓዝ የአቶ በላይ ቢነጋ መሬት ደንበር ላይ 11 ዲግሪ 41 ደቂቃ 53.4 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 10 ደቂቃ 28.2 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ስድስት፣
7. ከዚያም ከሞሰቢት ተራራ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመሄድ ከውጭባና የዕለት ድባና ቀበሌ ደንበር ላይ 11 ዲግሪ 41 ደቂቃ 43.6 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 10 ደቂቃ 20.3 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰባት፣

8. ከዚያም ከዕለት ድባና ቀበሌ ደንበር ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ጨዋ ደጋ አካባቢ ምንጩ ላይ 11 ዲግሪ 41 ደቂቃ 39.8 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 10 ደቂቃ 48.6 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ስምንት፣
9. ከዚያም ትንሽ ገደል አካባቢ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የእውነቴን እርሻ ወደ ውጭ በመተው 11 ዲግሪ 41 ደቂቃ 16.9 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 11 ደቂቃ 05.3 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ዘጠኝ፣
10. ከዚያም ጀብ መደብ ቦታ በመድረስ ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የእንግዳው እርሻ ወደ ውጭ በመተው 11 ዲግሪ 41 ደቂቃ 09.3 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 11 ደቂቃ 14.1 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስር፣
11. ከዚያም የዕለት ድባና ቀበሌ ደንበር በሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ አምቦ ጉጥ በመድረስ ጣኒጋው ላይ 11 ዲግሪ 41 ደቂቃ 38.5 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 11 ደቂቃ 2.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት አስራ ቁጥር አንድ፣
12. ከዚያም ከጣኒጋው በስተሰሜን አቅጣጫ በመጓዝ የእሱባለው ክንዴ እርሻ ወደ ውጭ በመተው ሌባ ዋሻ ላይ 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 03.4 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 11 ደቂቃ 57.2 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ሁለት፣
13. ከዚያም ከሌባ ዋሻ በስተሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመከተል መኪና መንገዱ ላይ 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 21.3 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 12 ደቂቃ 02.8 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ሦስት፣
14. ከዚያም ከመኪና መንገዱ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የሌባ ዋሻ ወንዝ ዳር በመከተል አስታውን ወደ ውስጥ በማስገባት ሰማ ንጉሴ ቤት ጥግ ላይ 11 ዲግሪ 41 ደቂቃ 45.3 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 12 ደቂቃ 09.8 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥርአስራ አራት፣
15. ከዚያም ከሰማ ንጉሴ ቤት ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ መኪና መንገዱን ዳር በመከተል ዋንቃ ራስ ላይ 11 ዲግሪ 41 ደቂቃ 46.1 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 12 ደቂቀ 31.2 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ አምስት፣
16. ከዚያም ከዋንቃ ራስ ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የዋለና የበለጠ ደኛውን እርሻ ወደ ውጭ በመተው ወርቅ ውኃ ላይ 11 ዲግሪ 41 ደቂቃ 01.3 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 12 ደቂቃ 21.0 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ስድስት፣

17. ከዚያም ከወርቅ ውኃ ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ ጅብ ዋሻ ላይ የመንጌን እርሻ ወደ ውጭ በመተው 11 ዲግሪ 40 ደቂቃ 54.0 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 12 ደቂቃ 03.0 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ስባት፣
18. ከዚያም ከጅብ ዋሻ ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ዕለት ድባና እና ዳት ጊዮርጊስ ቀበሌ ደንበር ላይ 11 ዲግሪ 40 ደቂቃ 33.5 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 12 ደቂቃ 04.2 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ስምንት፣
19. ከዚያም ከዳት ቀበሌ ደንበር ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የአየለ ሞላ እርሻ ወደ ውጭ በመተው ነጭ ሳር ላይ 11 ዲግሪ 40 ደቂቃ 39.1 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 12 ደቂቃ 31.0 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ዘጠኝ፣
20. ከዚያም በተመሳሳይ አቅጣጫ በመጓዝ ላሊበላ ዋሻ ላይ የአለባቸውን እርሻ ወደ ውጭ በመተው 11 ዲግሪ 40 ደቂቃ 35.2 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 12 ደቂቃ 51 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ፣
21. ከዚያም ከላሊበላ ዋሻ በተመሳሳይ አቅጣጫ በመከትል ኳኳቱን በማለፍ ጐንች የወጣቶች መሬት ድንበር ላይ 11 ዲግሪ 40 ደቂቃ 18.8 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 13 ደቂቃ 17.9 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ አንድ፣
22. ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ቀይ ገደል ላይ የእስቴ እና ላይ ጋይንት ወረዳ ደንበር ማለትም ዳት ጊዮርጊስ እና የቀበሌ 15 ደንበር ላይ 11 ዲግሪ 40 ደቂቃ 06.2 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 13 ደቂቃ 30.2 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ሁለት፣
23. ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የነ ጌታሰው እርሻን ወደ ውጭ በመተው ድንበሩ ላይ 11 ዲግሪ 40 ዲቂቃ 12.2 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 13 ደቂቃ 53.7 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ሦስት፣
24. ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ቀጋ በረት ላይ 11 ዲግሪ 39 ደቂቃ 52.5 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 14 ደቂቃ 35.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ አራት፣
25. ከዚያም በተመሳሳይ አቅጣጫ በመከተል ቀበሌ 10 መስብር ላይ የቢሰጥ እርሻን ወደ ውጭ በመተው 11 ዲግሪ 40 ደቂቃ 01.3 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 14 ደቂቃ 54.6 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ አምስት፣

26. ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የጠንፎ ዘመደ ማርያም ላይ 11 ዲግሪ 40 ደቂቃ 30.1 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 14 ደቂቃ 46 ሴክንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ስድስት፣
27. ከዚያም በተመሳሳይ አቅጣጫ በመከተል አስታውን ወደ ውስጥ በማስገባት ጥጆች መዋያ ላይ 11 ዲግሪ 41 ደቂቃ 12.7 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 14 ደቂቃ 25.8 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ሰባት፣
28. ከዚያም ከጥጆች መዋያ ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ ጅብ ገደል ላይ 11 ዲግሪ 41 ደቂቃ 26.5 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 14 ደቂቃ 48.3 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ስምንት፣
29. ከዚያም በተመሳሳይ አቅጣጫ በመከተል ገቨጋ ጎጥ ገሀው መሬት ላይ 11 ዲግሪ 41 ደቂቃ 22.7 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 15 ደቂቃ 18.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሀያ ዘጠኝ፣
30. ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ገቨጋ ላይ መንደሩን እና አስታውን ወደ ውጭ በመተው መንገዱ ላይ 11 ዲግሪ 41 ደቂቃ 43.9 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 15 ደቂቃ 14.2 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ስላሳ፣
31. ከዚያም በተመሳሳይ አቅጣጫ በመከተል ቁጢጥ ተራራ የግራርያ ወንዝ መነሻ ላይ 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 24.3 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 15 ደቂቃ 11.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ አንድ፣
32. ከዚያም ከቁጢት ተራራ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ዋሮ ደጋን አልፈን ቸሬ ባዶ ላይ 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 38.8 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 15 ደቂቃ 43.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ ሁለት፣
33. ከዚያም የምዕራብ አቅጣጫ በመከተል ሾተል ሜዳ ቀርጢት ወጋ ላይ 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 48.5 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 15 ደቂቃ 33.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ ሦስት፣
34. ከዚያም ከሾተል ሜዳ ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመጓዝ ሰማይ ሜዳ አባዶ ላይ 11 ደቂቃ 42 ደቂቃ 56.9 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 15 ደቂቃ 54.7 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ አራት፣

35. ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ሰማይ ሜዳ አምጀው ላይ 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 40.2 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 16 ደቂቃ 09 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ አምስት፣
36. ከዚያም ከሰማይ ሜዳ ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ የከብቱ መውረጃ መንገድ ላይ 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 48.1 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 16 ደቂቃ 33.8 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ ስድስት፣
37. ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ የቀበሌ 10 እና የቀበሌ 09 ደንበር ላይ 11 ዲግሪ 43 ደቂቃ 06.2 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 16 ደቂቃ 11 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ ሰባት፣
38. ከዚያም በተመሳሳይ አቅጣጫ በመከተል ትንሽ ባህር ሸሸ ላይ አስታውን ወደ ውስጥ በማስገባት 11 ዲግሪ 43 ደቂቃ 21.3 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 15 ደቂቃ 40.7 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ ስምንት፣
39. ከዚያም ከትንሽ ባህር ሸሸ ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ሰማት ጐጥ ንጉስ ድንጋይ ላይ 11 ዲግሪ 43 ደቂቃ 24.1 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 15 ደቂቃ 13.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ስላሳ ዘጠኝ፣
40. ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ሰማት ጐጥ ንጉስ ድንጋይ ላይ 11 ዲግሪ 43 ደቂቃ 45.6 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 14 ደቂቃ 57 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ፣
41. ከዚያም ከሰማት ጐጥ ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ ሌባ ማረጃ የጨፋ ወንዝ አናት ላይ 11 ዲግሪ 44 ደቂቃ 09.9 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 15 ደቂቃ 02 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ አንድ፣
42. ከዚያም በተመሳሳይ አቅጣጫ በመከተል ሌባ ማረጃ ቁስ ልዑለ-ቃል/ሎቃል/ ጐጥ ላይ 11 ዲግሪ 44 ደቂቃ 26 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 15 ደቂቃ 31.3 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ ሁለት፣
43. ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ ቀጋ መንደርን ወደ ውጭ በመተው ጓዲ ሳር ላይ 11 ዲግሪ 44 ደቂቃ 39.8 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 15 ደቂቃ 44.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ ሶስት፣

44.ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ባህር ዛፉን ወደ ውጭ በመተው ዋሮ ደጋ ጎንጭሊት ጦጥ ቀበሌ 04 ደንበር ላይ 11 ዲግሪ 44 ደቂቃ 52.2 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 15 ደቂቃ 26.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ አራት፣

45.ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ዋሮ ደጋ ገራገራ ዋሻ ላይ 11 ዲግሪ 44 ደቂቃ 44.7 ሴኮንደ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 15 ደቂቃ 11.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ አምስት፣

46.ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ዳሞት ጦጥ ሙቄት ላይ የፈንታ እርሻን ወደ ውጭ በመተው 11 ዲግሪ 44 ደቂቃ 55.7 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 14 ደቂቃ 50.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ ስድስት፣

47.ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ መስቀል አዛ ጦጥ ቁርጠት ውኃ ላይ 11 ዲግሪ 45 ደቂቃ 19.7 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 14 ደቂቃ 54.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ ሰባት፣

48.ከዚያም ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመከተል መስቀል አዞ ጦጥ መሀል ተራራ ላይ 11 ዲግሪ 45 ደቂቃ 13.2 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 14 ደቂቃ 34.1 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ ስምንት፣

49.ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ የቀበሌ 04 እና የአርጋ ድድም ቀበሌ ደንበር የጮለጌ ወንዝ መነሻ ላይ 11 ዲግሪ 44 ደቂቃ 58.8 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 14 ደቂቃ 05.6 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ ዘጠኝ፣

50.ከዚያም ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ አርጋ ጽዮን ጦጥ ነጭቱ ድንጋይ ላይ ከመንደሩ በላይ 11 ዲግሪ 45 ደቂቃ 26.5 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 14 ደቂቃ 03.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምሳ፣


51.ከዚያም በተመሳሳይ አቅጣጫ በመከተል ወገሬ ጦጥ እንቅልፊት ላይ 11 ዲግሪ 45 ደቂቃ 18.8 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 13 ደቂቃ 31.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምሳ አንድ፣

52.ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ የአርጋና የሞክሸ ቀበሌ ደንበርን በማለፍ ሜዳው ላይ 11 ዲግሪ 44 ደቂቃ 57 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 13 ደቂቃ 14.7 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምሳ ሁለት፣


53. ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ቡልጭት ውኃን በማለፍ ቁልፍ ቤት ላይ 11ዲግሪ 44 ደቂቃ 14.9 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 13 ደቂቃ 08.6 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምሳ ሶስት፣
54. ከዚያም ወደ ተመሳሳይ አቅጣጫ በመከተል ቅማሎት ላይ 11 ዲግሪ 43 ደቂቃ 48 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 13 ደቂቃ 23.9 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምሳ አራት፣
55. ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ርግብ ጐጥ የርብ ወንዝ መነሻ ከአስታው ስር 11 ዲግሪ 43 ደቂቃ 16.9 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 13 ደቂቃ 19.1 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምሳ አምስት፣
56. ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ከርብ ወንዝ መነሻ በላይ አስታውን ወደ ወጭ በመተው 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 52 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 13 ደቂቃ 29.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምሳ ሰድስት፣
57. ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ ልም ሣርን በማለፍ ብሆር ጎጥ ላይ 11 ዲግሪ 43 ደቂቃ 06.6 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 12 ደቂቃ 59.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምሳ ሰባት፣
58. ከዚያም ከብሓር ጎጥ ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመከተል ገደባ መውጫ መንገዱን ላይ 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 44.3 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 12 ደቂቃ 43.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምሳ ስምንት፣
59. ከዚያም ከገደባ መውጫ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ አምጃው ጎጥ ላይ 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 48.4 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 12 ደቂቃ 17 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምሳ ዘጠኝ፣
60. ከዚያም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ አምጃው ጎጥ በማለፍ ጉጉት ስፍራ ላይ 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 51.2 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 11 ደቂቃ 37.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ስልሳ፣
61. ከዚያም ወደ ተመሳሳይ አቅጣጫ በመከተል እንባቡት ላይ 11 ዲግሪ 43 ደቂቃ 00 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 11 ደቂቃ 22.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ስልሳ አንድ፣

62. ከዚያም ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ አምቦ ወንዝ ላይ 11 ዲግሪ 43 ደቂቃ 09.9 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 11 ደቂቃ 08.7 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ስልሳ ሁለት፣
63. ከዚያም ከአምቦ ወንዝ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ መኪና መንገዱን በማቋረጥ ሶራስ ቀበሌ ደንበር ሌባ ማረጃ ላይ 11 ዲግሪ 42 ደቂቃ 57.3 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 10 ደቂቃ 57.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ስልሳ ሶስት፣
64. ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመከተል ማደጉት ላይ 11 ዲግሪ 43 ደቂቃ 05.3 ሴኮንድ ሰሜን እና 38 ዲግሪ 10 ደቂቃ 38.8 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ስልሳ አራት፣ በመሆን ከልዋየ ድንበር መነሻ ቦታው ጉልት ቁጥር አንድ ጋር ዞሮ ይገጥማል።።

10.2. የጉና ተራራ ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ የክለላ ካርታ



10.3. የፀደቀ የቀበሌ ቃለጉባኤ (ናሙና ቀበሌ፡ ጥጥራ ዳሞት)



በደቡብ ጎንደር መስተዳደር ዞን በ ጎዛ 2037 ወረዳ በ ደምቀ ቀን 29/8/2005
ስፍራ እና የቀበሌውን ወሰን ክለላ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ፣ ቁ.04/ፕሮጀ/04 ቀበሌ የጉና ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ

የክለላው መነሻ ቦታ አዳክላ ዕድ ጓንሮ

የክለላ ስራው የተጀመረበት ቀን 29/8/2005

ክለላው የተጀመረበት ሰዓት 2:00

የስብሰባው ቦታ አሮጌ ቀበሌ ጓንሮ

የስብሰባው ቀን 29/8/2005

የስብሰባው ሰዓት 12:00

ተ.ቁ	ተሳታፊዎች	የስራ ድርሻ
1.	አቶ ዳኛቸው መኮ	የቀበሌ ዕላ ጥሪ አስተዳዳሪ
2	,, ገዛ አንዲሶ	,, ,, የሰላም አስተዳደር ባለሙ
3	ጎጃን ሌጅዲ ስሸር	,, ,, ዕቅድ ሰብሳቢ
4	ወሬት አመሬ መንሮ	,, ,, ጽሕፈት
5	ፀሐ አንገታ ባለሙ	,, ,, የአካባቢ ደህንነት
6	ፀሐ አብዮር አመሬ	,, ,, የአስመራ ጽሁፈቤ
7	አቶ ታከታች ቅያሙ	,, ,, ,, ,,
8	አቶ አመሬ አለሙ	,, ,, ,, ,,
9	,, ሰሎሚ ሃይሉሩ	,, ,, አስተዳደር ፀጥታ ሀርቄ
10	,, አመሬ አሊሬ	የለሚ ጋዛንት መርዳ ገ/ት/ጽ/ሠ ጋሻዲ
11	,, መሪጌ አመሬ	,, ,, ,, አስ/ፀጥታ ጋሻዲ
12	,, ሚተያለ አለሳ	,, ,, ,, አስ/ጽ/ሠ ተመስገን
13	,, ፎሌና ጎሸሰሌ	,, ,, ,, አስገ/ፕ/ሠ/አስ/አመ ገ/
14	,, መሪሳን መሐመድ ሚሊዩ	የአመክሮ ገ/ት/ፓ/ል/ሠ ሰብሳቢ
15	,, ቁናው አመሬ	,, ,, ,,
16	,, ጌታሁን አሊሚሁ	የፀ/ጽ/ዞን ገ/ት/መልሀቅ ገለጠላ
17		
18		

አለንበት።


አጀንዳ

በ04/ፕሮጀ/ሃሚ/ት ቀበሌ አስተዳደር በኩል የጉና ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራን ወሰን ለመከለልና ለማፀደቅ ፣

ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ የሚገኙትን የብዙሃ ሕይወት ሃብቶች ለመጠበቅ፣ ጤናማ ስርዓተ ምህዳ
ለመፍጠር፣ ዘለቂታ ባለው መንገድ ለመንከባከብ፣ ከቱሪዝም ሊገኝ ከሚችለው ሳይንሳዊ ጠቀሜታና የስራ ዕድ
ከመፍጠር አኳይ ታሳቢ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራው ያለው አስተዋፆ ከፍተኛ መሆኑን ስብሳቢው ሰፋ ያለ ማብራሪ
በመስጠት ከገለፁ በኋላ በተሰብሳቢዎች ተጨማሪ አስተያየት ተሰጥቶና ውይይት ተካሂዶ ታሳቢ ማህበረሰብ ጥብ
ስፍራውን መከለል እንዳለበት በመተማመን የወሰን ክላይ ኮሚቴው ያለምንም ልዩነት የሚከተለውን የውሳኔ ሃሳ
አስተላልፏል ።

የውሳኔ ሃሳብ

1. የታሳቢ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራውን ወሰን ከቀበሌው ለ/ምክር/ቤት አቅጣጫ ከቃለጉባኤ ቁ/አንቀጽ



2.ይህ የቀበሌው የታሳቢ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ወሰን ክለላ ቃለ ጉባኤ ከተወሰዱት የጅኦኤስ ኮርዲኔቶች ጋር ተያ
ለ..... ወረዳ አስተዳደር ፣ለአካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት፣ ለቀበሌ
አስተዳደርና ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ በቀበሌው ማህተም ተረጋ
አንዳንድ ኮፒ እንዲደርስና እንዲፀድቅ ባልተለያየ ድምፅ ተስማምተን በ...ቀን ከቀኑ በ...ሰዓ
የድንበር ክለላውንና የሪፖርት ሥራ አጠቃለናል ።

ተ.ቁ	የኮሚቴው አባላት ስም	ፊርማ
1.		
2		
3		
4.		
5		
6		
7		
8		
9		
10		
11		
12		
13		
14		
15		
16		
17		
18		

10.4. የጸደቀ የወረዳ ቃለ ጉባኤ (ናሙና ወረዳ: ላይ ጋይንት)

ቀን 27/09/2005 ዓ.ም

ላይ ጋይንት ወረዳ አስተዳዳር በተደረገው ስብሰባ

1. አቶ ሃይሌ አለነ	ፍትህ ጽ/ቤት ኃላፊ
2. አቶ አስፋ ሙልጌታ	ግብርና ጽ/ቤት ተወካይ
3. አቶ አደራጀው ወርቁ	አካ/ጥ/መ/አስ/አጠ/ጽ/ቤት ኃላፊ
4. አቶ አወቀ አራጌ	አስተዳደር እና ፀጥታ ጽ/ቤት ኃላፊ
5. አቶ ሲሳይ ምህረት	ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊ
6. አቶ መርሻ አበጀ	አሰ/ ጽ/ቤት ተወካይ
7. አቶ ጌታስው አዘዘ	ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ
8. አቶ ሀብታሙ በላቸው	ህብረት ስራ ማህበራት ጽ/ቤት ኃላፊ
9. አቶ ዮሴፍ ኃለስላሴ	ባህል፣ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ ባለሙያ
10.አቶ ብርሃነ መስቀል ዓለሙ	ባህል፣ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ ባለሙያ
11.አቶ ቀናው አበጀ	ባህል፣ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ ባለሙያ
12.አቶ ጌታስው ዓለም	ደቡብ ጎንደር ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ባለሙያ
13.አቶ ይታየው አለነ	የላይ ጋይንት ወረዳ አካ/ጥ/መ/አስ/አጠ/ጽ/ቤት ባለሙያ

አለንበት፡

አጀንዳ፡ የጉና ታሳቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ለማድረግ በ15(ደራ ቀፎየ)፣ 10(ጉና ገደባ)፣ 09(አቃቢት) እና 04(ጥጥራ ዳሞት) ቀበሌዎች የዳር ድንበር ክለላ ኮሚቴ የተለዩትን የዳር ድንበር ወሰን ምልክቶችን ማጽደቅ ነው፡፡

የጉና እና አካባቢው ተፈጥሮ ሃብት ተጠብቆ ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ እና የአካባቢው ህብረተሰብ ከሃብቱ በዘላቂነት እንዲጠቀም ለማስቻል በአራቱም ቀበሌዎች ህብረተሰቡን ያሳተፈ የዳር ድብንር ክለላ እና የወሰን ድንበር ልየታ ተካሂዷል፡፡ በሁሉም ቀበሌዎች የድንበር ክለላ ኮሚቴው የተፈራረመበት የስምምነት ቃለ ጉባኤ በእጃቸው ይገኛል፡፡ በፋረጣ እና እስቴ ወረዳዎች በኩልም እንደዚሁ የወሰን ድንበሩ ተለይቶ ቀርቧል፡፡

ስለሆነም አካባቢው በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራነት ተቋቁሞ በውስጡ የሚገኘው የብዝሃ ሕይወት ሃብት እና የውኃ ማማነቱ ተጠብቆ ለትውልድ ማቆየት ተገቢ በመሆኑ ይህ ጉዳይ ለክልሉ መንግስት ቀርቦ የሰው ኃይል መዋቅር፣ ጽ/ቤት እና በጀት ተፈቅዶለት አስተማማኝ ዋስትና እንዲያገኝ የተከለለ በመሆኑ የወረዳ አስተዳደሩ ከየቀበሌው የቀረበውን የክለላ ቃለ ጉባኤ ሰነድ ተቀብሎ እንዲያጽድቅ ተጠይቋል፡፡

በዚህ መሰረት፡-

የቀበሌ 15 ከወሰን መለያ ቁጥር 161-179

የቀበሌ 10 ከወሰን መለያ ቁጥር 179-338

የቀበሌ 09 ከወሰን መለያ ቁጥር 338-379

የቀበሌ 04 ከወሰን መለያ ቁጥር 379-420

የጉና ታላቢ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ የወሰን ክልል በላይ ኃይንት ወረዳ በኩል ያለፈባቸው የወሰን መለያ ቁጥሮች መሆናቸውን ተዘርዝረው ቀርበዋል፡፡ የቀረበውንም አጠቃላይ የእብርት ዞኑን የዳር ድንበር ወሰን ክለላ የተቀብለን ሲሆን ከአራቱም ቀበሌዎች የተወሰዱት የጅፒኤስ ንባቦች ወሰን መለያ ቁጥሮች ከዚህ በኋላ የቀበሌዎቹና የጉና የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ የወሰን ምልክቶች መሆናቸውን ያለምንም ልዩነት ተስማምተን አጽድቀናል፡፡